ቀን Date: መስከረም 2 1 2018
ቁጥር Ref.No: 3.0/112/18

በአባሪው ለተዘረዘሩት

በያሉበት

የአሰራር ስርዓት መላክን ይመለከታል

የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/95 ከሐምሌ 2017 ጀምሮ የተሰረዘ በመሆኑ የነባር የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮችን በተመለከተ በታክስ አስተዳደሩ ለሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም እንዲያግዝ የገቢዎች ሚኒስቴር የሽግግር የአሰራር ስርዓት ተዘጋጅቷል።

በዚሁ መሰረት የታክስ አስተዳደር ስራዎች በወጥነት እና በቅንጅት ለማስፈፀም እንዲረዳ የተዘጋጀውን የአሰራር ስርዓት ተፈርሞ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የአሰራር ስርዓቱን --- ገጽ በዚህ መሸኛ የላክን መሆኑን እንገልፃለን።

ከሰላምታ ጋር

አብዱረህማን ኢድ ጣሂር
ሚኒስትር ዴኤታ
የታክስ አጥሬሽን ዘርፍ



እንዲያውቁት

- ለክብርት ሚኒስትር

ግልባጭ

- ለሚንስትር ጽ/ቤት
- ለታክስ ስርዓት ዘርፍ
- ለኢ. ዳታ ዘርፍ
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል
- ለታክስ ከፋዮች ምዝገባና አገልግሎት ዳ/ት
- ለታክስና ጉምሩክ መረጃ ማብራሪያና የምክር አገ/ ዳ/ት
- ለታክስ ማጣጣምና ክለሳች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ማስታወቅ ዳይሬክቶት
- ለታክስ ዕዳ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት ዳይሬክቶት
- ለታክስ ሕግ ተገገርነት ስትራቴጂና ስጋት ሥራ አመራር ዳ/ት
- ታክስ መረጃና ሽያጭ መ/መ/ አስተዳደር ዳይሬክቶት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ገቢዎች ሚኒስቴር

CamScanner

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (በያሉበት)

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ቁጥር 1 ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለመካከለኛ ቁጥር 2 ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት

CamScanner

የክልል ገቢ ቢሮዎች

- ለትግራይ ገቢዎች ልማት ባለሥልጣን

  መቐሌ

- ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ሰመራ

- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ባሕር-ዳር

- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳደር የገቢዎች ቢሮ

  ፌንፌኔ

- ለሶማሌ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ጅግጅጋ

- ለሲዳማ ብሔራዊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ባለሥልጣን

  ሀዋሳ

- ለደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ

  ሚዛን አማን

- ለደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ

  አርባ ምንጭ

- ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ገቢዎች ቢሮ

  ቡታጅራ

- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ገቢዎች ባለሥልጣን

  አሶሳ

- ለጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ባለሥልጣን

  ጋምቤላ

- ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገቢዎች ቢሮ

  ሐረር

- ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ
- **አዲስ አበባ**
- ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ባለሥልጣን

  ድሬዳዋ

CamScanner

ገቢዎች ሚንስቴር

የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮችን ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ የሽግግር የአሰራር ሥርዓት

መስከረም

2018 ዓ.ም

CamScanner

ማውጫ

1 መግቢያ 3

2- ትርጉም 3

2.1 ግብር ከፋይ 3

2.2 የታክስ ከፋይ ምደባ 3

2.3 ምዕራፍ አንድ 3

2.5 ለተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ውሳኔ 4

2.6 የታክስ ዕዳ መክፈያ ጊዜ 5

3 ዓላማ 5

4 አስፈላጊነት 5

5 የተፈጻሚነት ወሰን 6

6 የታክስ ከፋይ መረጃ ማጥራትና ማደራጀት፣ 6

7 የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቅድመ ሁኔታ እና አፈጻጸም 8

8 የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት 9

8.2 የታክስ ማስታወቅ ተግባራት 10

8.3 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ ተግባራት 10

8.4 የደረሰኝ ህትመትና ስርጭት ቁጥጥር ተግባራት 10

9. የቅሬታ አፈታት ሥርዓት በተመለከተ 11

11 የአፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ እና ግምገማ ተግባራት ፣ 12

12 . የሪፖርት ይዘት 12

13 በዚህ የአሰራር ስርዓት ያልተሸፈኑ ጉዳዮች፣ 13

14 ይህ የአሰራር ሥርዓት የሚቆይበት ጊዜ 13

15 የአሰራር ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ የድርጊት መርሀግብር 13

ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ 14

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No.2

CamScanner

1 መግቢያ

ላለፉት 22 አመታት በስራ ላይ የነበረው የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 ከሐምሌ 2017 ጀምሮ የተሰረዘ በመሆኑ ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዘግበው የነበሩ ግብር ከፋዮችን (ድርጅቶችና ግለሰብ ነጋዴዎች ጨምሮ) በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ የወጣ መመሪያ ቁጥር 1104/2017 መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዘገብ የሚከናወኑ ዋና ዋና የታክስ አስተዳደር ተግባራት በወጥነት ለመፈጸም እንዲቻል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ይህ የአሠራር ሥርዓት ተዘጋጅቷል።

2-ትርጉም

2.1 ግብር ከፋይ

ግብር ከፋይ ማለት የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ድርጅት ወይም ግለሰብ ማለት ነው፡

2.2 የታክስ ከፋይ ምደባ

የታክስ ከፋይ ምድብ ማለት ከሐምሌ 2017 በፊት የተርን ኦቨር ታክስ ሲከፍል የነበር ግብር ከፋይን በተቀመጠው መሥፈርት መሰረት በምዕራፍ አንድ ወይም በምዕራፍ ሁለት መመደብ ማለት ነው።

2.3 ምዕራፍ አንድ

በምዕራፍ አንድ የተመደበ ግብር ከፋይ ማለት ከሐምሌ 2017 በፊት ለታክሱ የተመዘገበ ግብር ከፋይ ሆኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጁ ቁጥር1341/2016 አንቀጽ 15 እና በመመሪያ ቁጥር 1104/2017 አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው ቅድመ ሁኔታ በተጨማሪ፣

1. በ2017 በጀት አመት እና ወይም በፊት ባሉ የሂሳብ ጊዜያት የታክስ ማስታወቅ ግዴታውን በአብዛኛው በክፍያ የተወጣ፣
2. ከዕዳ ትራከር ቱል እና ከሲግታስ በተገኘ መረጃ ሊከፈል የሚገባ የታክስ ዕዳን የክፍያ ጊዜ ስምምነት ገብቶ ክፍያውን በመክፈል ላይ ያለ፣
3. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ወደ 15% ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔ ለማስቀየር ለሽያጭ ማዕከል የሚያቀርብ ስለመሆኑ ስምምነት የገባ፣
4. በQR-Code ያለው የማኑዋል የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ ያሳተመና የተረከበ ሆኖ ጥቅም ላይ ያልዋለውን የደረሰኝ ብዛት በጽሑፍ ያሳወቀ፣
5. በQR-Code ያለው የማኑዋል የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ ታትሞ ያልተሰራጨ በቅ/ጽ/ቤቱ ወይም ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የሚገኝ የተረከበ፣

CamScanner

6. የታክስ ከፋይ ምዝገባ ወቅታዊ ቋሚ የስራ አድራሻ፣ የስልክ ቁጥር፣ የባንክ አካውንት መረጃ ያስመዘገበ ወይም ወቅታዊ ያደረገ፣
7. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 ለታክሱ ስለመመዝገብ የተቀመጠው የ2,000,000 ሚ.ሊ.ያን ብር አመታዊ ሽያጭ ባይሞላም ታክስ የሚከፈልበት ሽያጭ ገቢ ያለው፣

2.4 ምዕራፍ ሁለት

በምዕራፍ ሁለት የተመደበ ግብር ከፋይ ማለት ከሐምሌ 2017 በፊት ግብር ከፋይ የነበረ ከታክስ ማስታወቅ እና ከታክስ ዕዳ ጋር በተያያዘ በተለያያ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሆኖ በዚህ የአሰራር ስርዓት መሰረት በሚደረግ የመረጃ ማጥራት ስራ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ ከዚህ በታች በተገለጸው፣

1. በ2017 በጀት አመት እና ከዚያ በፊት የታክስ ማስታወቅ ግዴታውን በተከታታይ ከ6 ወር በላይ ያልተወጣ እና በተደረገ ማጣራት ወደ ዘላቂ ማረፊያ እንዲገባ የተለየ ግብር ከፋይ፣
2. ከ2016 በጀት አመት ጀምሮ ለሁለት አመታት በተከታታይ ባዶ የተርንኦቨር ታክስ ታክስ ማስታወቂያ ያቀረበ፣
3. በተለያያ ደረጃ ላይ የሚገኝ የታክስ ዕዳ ያለበትና በክትትል የታክስ ዕዳውን ለማስከፈል ያልተቻለ፣ በክፍያ ጊዜ ስምምነት መሰረት ክፍያ ያልፈጸመ፣
4. የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያውን ያላሳደሰ፣
5. በQR-Code ያለው የማኑዋል የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ ለማሳተም ጥያቄ ያለቀረበ፣
6. ባስመዘገበው የስራ አድራሻ ያልተገኘ፣ባስመዘገበው ስልክ ቁጥሩ ማግኘት ያልተቻለ፣የሂሳብ መዝገብ፣ የባንክ አካውንት እና የመረጃ ለውጥ ማድረጉን ያላሳወቀ ወይም ወቅታዊ ያላደረገ፣
7. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ቁጥር 1341/2016 እና በመመሪያ ቁጥር 1104/2017 መሠረት ታክስ የሚከፈልበት ሽያጭ ያለው ስለመሆኑ ቀጣይነት ባለው መልኩ በአስተማማኝ ማስረጃ ማስረዳት የማይችል እንዲሁም ሌሎች በአዋጁ የተመላከቱትን በቅድመ ሁኔታ የማያሟላ ግብር ከፋይ ነው።

2.5 ለተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ውሳኔ

ለተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ውሳኔ ማለት የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዩ አስቀድሞ (በግብር ከፋዮች ምዝገባ፣ በታክስ ማስታወቅ፣ በታክስ ዕዳ አስተዳደር በታክስ መረጃ አስተዳደር / የደረሰኝ ህትመትና ስርጭት ስራ ክፍል፤ ከስግታስ ሲስተም ወ.ዘ.ተ) በዚህ የአሰራር ስርዓት መሠረት መረጃው ተጣርቶ በሚመለከተው ስራ ክፍል በቀረበ መነሻ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በታክስ አፕሬሽን ወይም በታክስ ሥርዓት ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ ወይም በክልል/ከተማ

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

CamScanner

አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ባለው ተመሳሳይ ተግባር የሚያከናውን አደረጃጀት በምዕራፍ አንድ እና በምዕራፍ ሁለት ስር በተመደበ ግብር ከፋይ ላይ በታክስ ባለሥልጣኑ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ ወይም አለመመዝገብ በተመለከተ የሚሰጥ ውሳኔ ነው።

2.6 የታክስ ዕዳ መክፈያ ጊዜ

የታክስ ዕዳ መክፈያ ጊዜ ማለት በታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 179/2015 ወይም በክልል/ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ባለው መመሪያ መሰረት በመረጃ ማጥራት የተለየ ግብር ከፋይ ሆኖ የታክስ ዕዳውን ለመክፈል በታክስ ዕዳ አስተዳደር ስራ ክፍል ተጣርቶ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሃላፊ ወይም በዋና መ/ቤት የሚሰጠው የታክስ መክፈያ ጊዜ ነው።

3 ዓላማ

ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም በፊት የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የነበሩ ግብር ከፋዮችን በማጣራት በወጥነት ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት ማሸጋገር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ለመዘርጋት ነው።

4 አስፈላጊነት

1) በአዋጅ ቁጥር 1341/2016 እና በመመሪያ ቁጥር 1104/2017 መሰረት የሚከናወኑ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ የመረጃ ማጥራት ስራዎች ወጥነት ባለው ሁኔታ ለመፈጸም፣
2) የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የነበረ ግብር ከፋይ የታክስ አካውንት ተጣርቶ እንዲዘጋ በማድረግ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ፣
3) ለተርን ኦቨር ታክስ ተመዝግቦ የነበረ ግብር ከፋይ አስመልክቶ የስራ ቅንጅት እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ለማድረግ፣
4- የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ ለነበረ ግብር ከፋይ የተእታ ምዝገባ አገልግሎት አሰጣጡን ግልጽ እና ቀልጣፋ በማድረግ በፊዴራል፣ በክልልና በከተማ አስተዳደር የገቢ ሰብሳቢ አካላት የተናበበ አሰራር ለመዘርጋት ማስቻል ነው።

CamScanner

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2 Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

5 የተፈጻሚነት ወሰን

ከሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1395/2017 የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 የተሻረ በመሆኑ ከሐምሌ 1 ቀን 2017 በፊት የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ በነበሩ ግብር ከፋዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ነው፡፡

6 የታክስ ከፋይ መረጃ ማጥራትና ማደራጀት፣

የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የነበረን መረጃ ለማጥራት ለመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት ከሲግታስ መረጃው እንዲወርድ በማድረግ መረጃው ዝግጁ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. በገቢዎች ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት በሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች የቅርብ ድጋፍ እና ክትትል በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣በክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢ ቢሮዎች የመረጃ የማደራጀትና የመተንተን ስራ ለማከናወን መረጃው፣
   - ❖ ግብር ከፋይ ስም፣
   - ❖ በግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
   - ❖ ወርሀዊ ወይም የሩብ አመት የታክስ ማሳወቂያ በተከታታይ ባዶ ያሳወቁ እና ያላሳወቁ፣
   - ❖ በታክስ ዕዳ ገንዘብ መጠን፣
   - ❖ መሠረታዊ የምዝገባ መረጃ (ቋሚ የስራ ቦታና የስልክ) አድራሻ ወ.ዘ.ተ
2. የክልልና ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ 50 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 እንደተገለጸው የደረጃ ለ ግብር ከፋዮች በጠቅላላ የሽያጭ ገቢያቸው ላይ በግብር ማስከፈያ መጣኔ መሠረት አመታዊ ግብራቸውን የሚከፍሉና የተጨማሪ እሴት ታክስ የግዴታ ምዝገባ የማይመለከታቸውን ታክስ ከፋዮች በመለየት መረጃ ማደራጀት፣
3. ታክስ ከፋዩ በተለያየ ምክንያት ሁለት የታክስ አካውንት ለተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ያላቸውን መረጃ ማጣራትና ማደራጃት፣
4. ታክስ ከፋዩ ከሐምሌ ወር 2017 ዓ/ም በፊት የታክስ ውሳኔ ደርሶት በየደረጃው ባሉ በፍርድ ቤት በክርክር ላይ ያለ ከሆነ ከታክስ ዕዳ ትራከር ቱል በማጣራት ዕዳው እንዲከፈል ወይም የክፍያ ስምምነት እንዲገባ ለማድረግ ለይቶ ለማወያየት እንዲያስችል መረጃውን ማደራጀት ፤

CamScanner

5. ከስድስት ወር በላይ ታክስ ያላሳወቀ፣ በባዶ (ሽያጭ እንደሌለው) ያሳወቀ ግብር ከፋይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከመመዝገብ በፊት በቀጣይ ሃላፊነቱን ለመወጣት ስለመቻሉ ለማረጋገጥ የሚያስችል መረጃውን ማደራጀት፤
6. ከሐምሌ 1 2017 ዓ/ም በፊት ለተርን ኦቨር ታክስ QR code ያለው ማንዋል ደረሰኝ የህትመት ፍቃድ ወስዶ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ህትመቱ ያልተከናወነ ግብር ከፋይ መረጃውን ማደራጀት፣
7. QR code ያለው የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ አስቀድሞ የታተመና ጥቅም ላይ ያልዋለ መረጃ ታክስ ከፋዩ ማረጋገጫ እንዲያቀርብ በማድረግ ማደራጀት፣
8. ታትሞ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ በቅ/ጽ/ቤቶች ወይም በክልል/ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን በመጋዘን ያለ ያልተሰራጨ የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ መረጃ በየግብር ከፋዩ ያልተሰራጨውን ደረሰኝ መረጃ ማደራጀት፣
9. በእጃቸው QR code የሌለው የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ ያላቸው ግብር ከፋዮችን በሚተላለፈው ጥሪ ወይም በቅ/ጽ/ቤቶች ወይም የክልልና ከተማ አስተዳደር ገቢ ቢሮዎች ከሚሰጡ አገልግሎት ጋር በማያያዝ ደረሰኙ እንዲያስወግዱ በማድረግ መረጃውን ማደራጀት፣
10. ለህትመት ለብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የታዘዘ ደረሰኝ ሆኖ ህትመቱ የተቋረጠውን በተመለከተ ለህትመቱ አስቀድሞ የተከፈለው ቅድመ ክፍያ የባንክ ስሊፕ እንዲቀርብ በማድረግ ለተጨማሪ እሴታ ታክስ ደረሰኝ ህትመት እንዲውል በማድረግ መረጃውን ማደረጀት፣
11. ከሐምሌ 1 /2017 ዓ.ም በኃላ ጥቅም ላይ በዋለ የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ የሽያጭ ገቢን ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲያሳውቅ እና ገቢው እንዲሰበሰብ በማድረግ መረጃውን ማደራጀት፣
12. የሽ/መ/መ/ በእጃቸው ያለ ግብር ከፋይ ሆነው በመመሪያው መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ የሽ/መ/መውን አስቀድመው ማሽኑን ለአቅራቢ ወይም ለጥገና ማዕከል አቅርበው የታክስ መጣኔው ወደ 15 በመቶ ለማስቀየር ስምምነት የገቡትን፣ በስምምነቱ መሰረት የታክስ ምጣኔውን ያስቀየሩትን መረጃ ማደራጀት፣
13. በመረጃ ማጥራት ውጤት መሰረት ተጣርቶ የሚፈለግ የታክስ ዕዳ የሌለባቸውን ታክስ ከፋዮች የታክስ አካውንት እንዲዘጋ፣ በሲግታስ የታክስ ዕዳ ሆኖ የሚታይ ቢሆንም የሚሰረዝ የታክስ ዕዳ መሆኑ ተጣርቶ መረጃው እንዲሰረዝ በማድረግ መረጃውን ማደራጀት፣

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር ሰነድ መዝገብና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2

CamScanner

14. **በምዕራፍ አንድ እና በምዕራፍ ሁለት የተመደቡ ግብር ከፋዮች በዚህ የአሰራር ስርዓት መሠረት በተደረገ መረጃ ማጥራት የተለዩ ግብር ከፋዮች በአዋጅ ቁጥር 1341/2016 እና በመመሪያ ቁጥር 1104/2017 መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ / የስምምነት ሰነድ/ ፎርም እንዲሞሉ በማድረግ ማደራጀት፣**

7 የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቅድመ ሁኔታ እና አፈጻጸም

1) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የክልልና ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን በመመሪያ ቁጥር 1104/2017 አንቀጽ 3 መሠረት በ30 ቀናት ውስጥ **በምዕራፍ አንድ** ስር የተለዩ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮችን ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

2) **በምዕራፍ ሁለት ተለይተው** የተመደቡ ግብር ከፋዮችን መረጃው ተጣርቶ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት የሚያከናውኑ መሆኑ የተረጋገጠ የተርን ኦቨር ታክስ ከፋይ የግብር ከፋዮች ብዛት መሠረት በማድረግ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፣ የክልልና ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣናት በሚወጣው መርሃ ግብር መሠረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ሊመዘገቡ የሚገባቸው የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮችን መረጃ አጣርቶ ወይም ዓመታዊ ጠቅላላ ሽያጭ መረጃ አሰባስቦ የመመዝገብ ሂደቱ ይህ አሰራር ስርዓት ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ መጠናቀቅ አለበት፡፡

3) ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተገለጸው ቢኖርም በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016 አንቀጽ 12 (2) ታክስ የሚከፈልበት ግብይት 2 ሚሊየን እና ከዚያ በላይ በመሆኑ የመመዝገብ ግዴታ የነበረበት ማንኛውም ሰው ለመመዝገብ ግዴታ ከሚኖርበት ቀን አንስቶ በ7 ቀን ውስጥ ማመልከቻ ያላቀረበ መሆኑ ሲረጋገጥ በአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 (ለ) መሠረት የታክስ ባለስልጣኑ የምዝገባ ግዴታ ከተጣለበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

4) በመረጃ ማጥራቱ በተደራጀው መረጃ የክልልና ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን ቀደም ሲል ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ ሆነው በገቢ ግብር ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1395/2017 አንቀጽ 50 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 እንደተገለጸው በጠቅላላ ሽያጭ ገቢያቸው መሠረት ግብር የሚከፈሉ **የደረጃ-ለ** ግብር ከፋዮች ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ በወጣው መመሪያ ቁጥር 1104/2017 አንቀጽ 2(2) መሠረት የተጨማሪ እሴት ታክስ የግዴታ ምዝገባ

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2
CamScanner

የማይመለከታቸውን በፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ ያልፈለጉ እና ምዝገባው እንዲሰረዝላቸው የሚጠይቁትን ከታክሱ ተመዝጋቢነት እንዲሰረዙ ማድረግ፡፡

5) ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበ አዲስ የተመዘገቡ ታክስ ከፋይ የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ መሆኑ በስምምነት ሰነድ ማረጋገጫ እየቀረበ፣-

5.1 የታክስ ከፋዩ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ማመልከቻ በ7 ቀን ካቀረብ ባለስልጣኑ ለታክሱ መመዝገቡ እንዳለበት ሲያምንበት፣

5.2 የታክስ ከፋዩ ወይም አመልካቹ ታክሱ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት ቋሚ አድራሻ፣ የኢንተርኔት አድራሻ፣ የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻ ወይም ሌላ ግብይት የሚያደረግበት የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም ግብይት የሚያከናውንበት አድራሻን ማቅረቡ ሲያረጋገጥ፣

5.3 የታክስ ከፋዩ ለታክሱ ስለመመዝገቡ በሚጠቀመው ማህበራዊ ሚዲያ እና በሚጠቀማቸው ኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ለማሳወቅ ወይም ለመለጠፍ የተስማማ መሆኑን ሲያረጋገጥ፣

5.4 ታክስ ከፋዩ በአዋጁ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በታክስ አስተዳደር አዋጁ መሰረት ከተመዝጋቢነቱ ጋር በተያያዘ ለውጥን በ30 ቀናት ለማሳወቅ ስምምነቱን ሲገልጽ፣

5.5 ለታክሱ የተመዘገበው ታክስ ከፋይ ታክሱ የሚከፈልበትን ግብይት ሲያቆም በአዋጁ አንቀጽ 17 ከምዝገባው ለመሰረዝ ማመልከቻ ለማቅረብ ስምምነቱን ሲገልጽ፣

እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

8 የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

8.1 QR code ያለው የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ አጠቃቀም፣

8.1.1 ከላይ በታክስ ከፋይ መረጃ ማጥራትና ማደራጀት ርዕስ ስር በተ.ቁጥር 7 እና 8 በተገለጸው መሰረት ጥቅም ላይ ያልዋለውን ደረሰኝ ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበው ታክስ ከፋይ ርዕሱን የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ፣ማስከፈያ ምጣኔውን 15% እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥሩን የአቅራቢው መረጃ ከተገለጸበት በታች በእስኪቢርቶ በመጻፍ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ግብይት ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

CamScanner

8.1.2 ታክስ ከፋዩ የተጨማሪ እስት ታክስ ደረሰኝ ታትሞ እንደተረከበ ባለው አሰራር መሰረት ቀሪው ደረሰኝ እንዲወገድ ይደረጋል፣

8.2 የታክስ ማስታወቅ ተግባራት

8.2.1 ከሐምሌ ወር 2017 ዓ/ም በፊት በተለያየ ምክንያት ታክሳቸውን ያላሳወቁት የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች እንዲያሳውቁ የተደረጉ ግለሰብ ወይም ድርጅት ግብር ከፋዮች ዝርዝር፣

8.2.2 ባዶ የሚያሳውቁ እና በማሳወቂያ ጊዜያቸው ያላሳውቁ ግብር ከፋዮች ዝርዝር፣

8.2.3 ከሶስት የሂሳብ ጊዜ በላይ ያላሳወቀ፣ በባዶ (ዜሮ) የሚያሳውቁ ግለሰብ ወይም ድርጅት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ግዴታውን መወጣት መቻሉን ማረጋገጥ፤

8.2.4 የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ከተሰረዘ በኃላ የተሰበሰበ የታክስ ገቢ አስታውቀው የከፈሉ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በመረጃ ማጥራቱ የተለየ ተሰብስቦ ያልተከፈለ ታክስ እንዲከፈል የታክስ ውሳኔ በማውጣት እንዲከፈል ማድረግ፣

8.3 የታክስ ዕዳ አሰባሰብ ተግባራት

8.3.1 ከሐምሌ ወር 2017 ዓ/ም በፊት የታክስ ዕዳ ያለባቸውን ድርጅቶች ዝርዝር መረጃ በታክስ ክፍያ ማራዘሚያ መመሪያ ቁጥር 179/2015 መሰረት በተሰጠ ውሳኔ የታክስ ዕዳ ያለባቸውን ግብር ከፋይ ድርጅቶች መረጃ በማጥራት ማደራጀት፣

8.3.2 በተራ ቁጥር 8.2.1 መሰረት በተጣራው መረጃ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ግብር ከፋዩ እንዲከፍል ወይም የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል የገቡ ግብር ከፋዮች ዝርዝር፣

8.3.3 በመረጃ ማጣራት ሂደት ሊሰበሰቡ የማይችሉትን የታክስ ዕዳዎች ዝርዝር በተመለከተ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ ፣

8.4 የደረሰኝ ህትመትና ስርጭት ቁጥጥር ተግባራት

8.4.1 ከሐምሌ ወር 2017 ዓ/ም በፊት የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ ህትመት ፍቃድ ተሰጥቷቸው QR code ያለው ደረሰኝ አሳትመው በእጃቸው ደረሰኝ ያላቸውን እና ታትሞ በማተሚያ ቤቱ የሚገኝ ያልተሰራጨ ደረሰኝ ብዛት በግብር ከፋይ መረጃውን በማጣራት ማደራጀት፣ለግብር ከፋይ እንዲሰራጭ ማድረግ፣

Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation

CamScanner

8.4.2 በተ.ቁ 8.4.1 መሰረት የተጣራ ያልተሰራጨ እና ጥቅም ላይ ያለዋለ የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ QR code ያለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እሰ.ኪ.ታተም ድረስ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አሰባበሰብ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደውን የደረሰኝ አይነት እና ብዛት መረጃ በማደራጀት ለመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ማቅረብ፣

8.4.3 በእጃቸው QR code የሌለው የተርን ኦቨር ታክስ ደረሰኝ ያላቸው ግብር ከፋዮችን ደረሰኙ እንዲወግድና የደረሰኝ ማስወገድ ተግባሩ አፈጻጸም ዝርዝር መረጃ ማደራጀት፣

8.5 የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል በኩል የሚከናወኑ ተግባራት

8.5.1 ለተጨማሪ እስት ታክስ የተመዘገበ ሰው ሆኖ ከተርን ኦቨር ታክስ ጋር በተያያዘ ከሐምሌ 2017 በፊት ሊከፈል ሲገባ ያልተከፈለ ውዝፍ የታክስ እዳ ወይም አስታውቆ መክፈል ያለበት ያልተከፈለ ወይም በትክክል ያልተከፈለ መሆኑ በመረጃ ማጥራት በተገኘ መረጃ ተጨማሪ ታክስ እንዲከፈል ሲወሰን በቀጣይ ጊዜያት በሲስተም የተርን ኦቨር ታክስ ገቢ ለመሰብሰብ የሚያስችል እና መረጃ የሚያዝበት ሁኔታ በመረጃ ቴክኖሎጂ መፍትሔ መስጠት፣

8.5.2 QR code ያለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ እሰ.ኪ.ታተም ድረስ ጥቅም ላይ ያለዋለ QR code ያለው የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አሰባበሰብ ጥቅም ላይ እንዲውል የተፈቀደ በመሆኑ የህትመት መረጃ እና ለተጨማሪ እስት ታክስ ገቢ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋለውን መረጃ የሚያዝበትና መረጃው የሚናበብበት ሁኔታ በመረጃ ቴክኖሎጂ መፍትሔ መስጠት፣

9. የቅሬታ አፈታት ሥርዓት በተመለከተ

9.1 በዚህ የአሰራር ስርዓት በዝርዝር ከተመላከቱት ተግባራትና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በግብር ከፋይ የሚቀርብ ቅሬታ በ10 ቀናት ውስጥ ስራው በሚመለከታቸው ስራ ክፍሎች (የታክስ ከፋዮች ምዝገባ፣ የታክስ ማስታወቅ፣ የታክስ ዕዳ አስተዳደር እንዲሁም የደረሰኝ ህትመትና ስርጭት፣ የመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ወ.ዘ.ተ) ባለሙያዎች ተጣርቶ በቀርበ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ቀጥሎ ባለ የሥራ ሃላፊ በተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ግብር ከፋይ ቅሬታውን በጽሁፍ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የታክስ አፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቅርቦ ውሳኔ

CamScanner

ይሰጥበታል፤ በውሳኔ ያልተስማማ ግብር ከፋይ ቅሬታውን ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ያቀርባል ::

9.2 ጉዳዩ በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ እልባት ያላገኘ ከሆነ ግብር ከፋይ ቅሬታውን ለታክስ አፕሬሽን ዘርፍ አቅርቦ ውሳኔ ያገኛል::

10.በክልል/ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን ከላይ ከተራ ቁጥር 8 እና 9 ያለውን የሚከናወኑ ተግባራት በታክስ ባለስልጣኑ ባለው ተመሳሳይ አደረጃጀት ተፈጻሚ የሚደረግ ይሆናል::

11 የአፈጻጸም ሪፖርት አቀራረብ እና ግምገማ ተግባራት ፣

11.1 በዚህ የአሰራር ስርዓት በተላለፈ ዝርዝር መረጃ መሰረት የተከናወኑ ዝርዝር ተግበራት ሳምንታዊና የወር የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አፈጻጸም በታክስ አፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ሥራ አስኪያጆች በኩል የተገመገመ ሪፖርት ለታክስ አፕሬሽን ዘርፍ ይልካል፤

11.2 የክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢ ቢሮዎች ሳምንታዊ እና የወር የተገመገመ የአፈጻጸም ሪፖርት ለገቢዎች ሚንስቴር የክልሎች ድጋፍና ታክስ ማጣጣም ዳሬክቶሬት ያስተላለፋል፤

11.3 የታክስ አፕሬሽን ዘርፍ ስለአፈጻጸሙ በ15 ቀን ግብረ መልስ ይሰጣል::

12. የሪፖርት ይዘት

12.1 የነባር የታክሱ ከፋይ ወቅታዊ መረጃ የተደረጀላቸው ሪፖርት

12.2 የታክስ ዕዳቸውን የከፈሉ ወይም ክፍያ ስምምነት የተሰጣቸው ዝርዝር፣

12.3 የደረሰኝ ህትመት በተመለከተ መረጃ ተጣርቶ የተወገደላቸው ዝርዝር

12.4 የታክስ አካውንት መረጃ ተጣርቶ የተሰረዘ የታክስ አካውንት ድርጅቶች ዝርዝር፣

12.5 በተጨማሪ እሴት ታክስ ስለመመዝገብ ቅሬታ ቀርቦ ምላሽ የተሰጣቸው ዝርዝር፣

CamScanner

12.6 ሌሎች ከታክስ አስተዳደር ስራዎች ጋር በተያያዘ በአስተዳደራዊ ሁኔታ ቀርበው ምላሽ የተሰጣባቸው ጉዳዮች ዝርዝር አባሪ በተደረገው ሪፖረት ማቅረቢያ ቅጽ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

13 በዚህ የአሰራር ስርዓት ያልተሸፈኑ ጉዳዮች፣

በዚህ የአስራር ሥርዓት ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በተመለከተ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወይም በክልል/ከተማ አስተዳደር የታክስ ባለስልጣን በተገኘ የትንተና መረጃ እና ሪፖርት መነሻነት በቀጣይ መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃ አስመለክቶ በዋና መ/ቤት የሚመለከታቸው ስራ ክፍሎች የውሳኔ ሃሳብ ቀርቦ በበላይ አመራሩ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይደረጋል፣

14ይህ የአሰራር ሥርዓት የሚቆይበት ጊዜ

ይህ የአሰራር ስርዓት ተፈርሞ ከተላላፈበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 6 ወራት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡

15 የአሰራር ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀ የድርጊት መርሀግብር

የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮችን ወደ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሸጋገር		
ተ.ቁ	የሚከናወነው ተግባር	የሚፈጸምበት ጊዜ
1	የተርን ኦቨር ታክስ ግብር ከፋዮች የታክስ ዕዳ መረጃ ማጥራት	ከነሃሴ 27/2017 ጀምሮ
2	የተርን ኦቨር ታክስ ግብር ከፋይ የምዝገባ ወቅታዊ መረጃ ማደራጀት	ከነሃሴ 27/2017 ጀምሮ
3	የተርን ኦቨር ታክስ ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እስት ታክስ ምዝገባ ማከናወን	እስከ መስከረም 27/2018
4	የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሕትመት ጥያቄ ማቅረብ	ከነሃሴ 27/2017 ጀምሮ
5	የተርን ኦቨር ታክስ ግብር ከፋዮችን የሽ/መ/መ ወደ ተእታ 15 በመቶ ማስቀየር	ከነሃሴ 27/2017 ጀምሮ
6	የተርን ኦቨር ታክስ ግብር ከፋዮች የቲኦቲ ደረሰኝ ማስወገድ	ከነሃሴ 27/2017 ጀምሮ
7	የተጨማሪ እሴት ታክስ ታክስ አካውንት የተከፈተላቸው መረጃ አጣርቶ የተርን ኦቨር ታክስ አካውንት መዝጋት	ከመስከረም 2018 ጀምሮ
8	ሳምንታዊና ወርሀዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ማስተላለፍ	ከመስከረም 2018 ጀምሮ

CamScanner

አባሪ 1

ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

የ .....ቅ/ጽ/ቤት/ክልል /ከተማ አስተዳደር ታክስ ባለስልጣን

ከ /2018 እስከ /2018 ድረስ

ተ.ቁ	የተከናወነ ተግባር	ክንውን		እስከ ሪፖርት ጊዜው የተከናወነ ብዛት	መግለጫ /ማስታወሻ
		እቅድ	አፈጻጸም		
1					
2					
3					
4					
5					

CamScanner

አባሪ-2

የታክስ ከፋይ የምዝገባ የስምምነት ቅጽ

እኔ አቶ---------- የ---------- ድርጅት ሥራ አስኪያጅ/ ፋይናንስ ሃላፊ/ ህጋዊ ወኪል ድርጅቱ ከነባር የተርንኦቨር ታክስ ተመዝጋቢነት ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት በሚያደረገው ሽግግር በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ መሰረት ከተርንኦቨር ታክስ ከፋይነት ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ለታክሱ ስለመመዝገብ በተዘረጋው አሰራር ስርዓቱ መሰረት በሚደረገው የመረጃ ማጥራት ውጤት በአዋጅ ቁጥር 1341/2016 እና በመመሪያ ቁጥር 1104/2017 መሰረት ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለመመዝገብ ለምዝገባ መሟላት ያለባቸውንና ሌሎች ከዚህ በታች የተጠቀሱትን፣

1. በተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ የተሰበሰበ ገቢን በማሳወቅ ለመክፈል፣
2. ታክሱ የሚከፈልበትን የስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውንበት ቋሚ አድራሻ፣ የኢንተርኔት አድራሻ፣ የማህበራዊ ሚዲያ አድራሻ ወይም ሌላ ግብይት የሚያደረግበት የኤሌክትሮኒክ ዘዴን በመጠቀም ግብይት የሚያከናውንበት አድራሻን ለማሳወቅ ወይም ወቅታዊ ለማድረግ፣
3. ለታክሱ ስለመመዝገቡ በሚጠቀመው ማህበራዊ ሚዲያ እና በሚጠቀማቸው ኤሌክትሮኒክ ዘዴዎች ለማሳወቅ ወይም ለመለጠፍ ፣
4. የሽ/መ/መ ምጣኔ ከተርንኦቨር ታክስ ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ 15% ምጣኔ ለማስቀየር፣
5. በድርጅቱ እጅያለ QR Code የሌለው ያልተሰራበት የተርንኦቨር ታክስ ደረሰኝ ለማስወገድ፣
6. ከተርንኦቨር ታክስ ወደ ተጨማሪ እሴት ታክስ በሚደረገው ሽግግር ለአዲት የሚፈለጉ የሂሳብ ሰነዶችን በውቅቱ ለማቅረብ፣
7. ከላይ በዝርዝር የተገለጸውን ለማሟላት የተስማማው መሆኑን በመግለጽ ይህን የስምምነት ሰነድ በድርጅቱ ውስጥ ባለኝ የስራ ሃላፋነት ወይም በተሰጠኝ ህጋዊ ውክልና መሰረት ተስማምቼ የስምምነት ሰነዱን መፈረሜን አረጋግጣለው።

በድርጅት በኩል	በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል
ስም	ስም
ፊርማ	ፊርማ
ቀን	ቀን
ማህተም	ማህተም

CamScanner